

# ዳዊትና ጎልያድ

* ጎልያድ ጌት ከሚባል የፍልስጥኤም አካባቢ የመጣ ፍልስጥኤማዊ ወታደር ነበር። ቁመቱም ስድስት ክንድ ከስንዝር የሆነ ነበር። ከእርሱ ጋራ ሊዋጋ የሚችል ምንም እስራኤላዊ እንደሌለና እርሱ ድል እንደሚያደርጋቸው ያለማቋረጥ ይፎክር ነበር። እርሱ ጋር ለመዋጋት የደፈረ አንድም እስራኤላዊ  ወታደር አልነበረም። እጅግ በጣም ፈሩት እንጂ።

ዳዊት እግዚአብሔርን የሚፈራ ትንሽ እረኛ ልጅ ነበር። “ከአንበሳና ከድብ መንጋጋ ያዳነኝ እግዚአብሔር ከዚህ ፍልስጥኤማዊ እጅም ያድነኛል።” አለ። ዳዊት ወንጭፍና አምስት ድንጋዮች ከምንጭ ወሰደ። ከዚያም ፍልስጥኤማዊውን ለመዋጋት ሄደ።

* ንጉስ ሳኦልም ዳዊትን የገዛ ራሱን ልብስ ሊያለብሰውና በራሱም ላይ የናስ ቍር ሊደፋለት፥ ጥሩርም ሊያለብሰው አሰበ። ሞከረም።

በተጨማሪም ትልቅ ሰይፍ ሊሰጠው ሞከረ። ዳዊትም ግን እነኝህን ሊጠቀምባቸው አልፈለገም። የእርሱ ብርታትና ጥበቃ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ ያውቃልና።

*  ጎልያድም እርሱን ሊዋጋ የመጣውን ዳዊትን ረገመው። ዳዊትም “አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ መጣህብኝ፤ እኔ ግን በተገዳደርከው በሠራዊት ጌታ በልዑል እግዚአብሔር በእሥራኤል አምላክ ስም እመጣብሃለሁ።” አለው።

* ከከረጢቱ አንድ ድንጋይ አወጣ። ወንጭፉ ውስጥ አስቀመጠና ወረወረ።   ጎልያድን ግንባሩን መታው። ጎልያድም በግንባሩ ተደፋ። ከዚያም ዳዊት የጎልያድን ሰይፍ ወሰደና ጎልያድን ገደለው።

* ዳዊት በእግዚአብሔር አመነ። እግዚአብሔርም ግዙፉን ፍልስጥኤማዊ ድል እንዲያደርገው ረዳው።

*የዳዊትና የጎልያድ ታሪክ የሚገኘው በ1ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 17 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com